# የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ ያወጣው

# የአቋም መግለጫ፤

የኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 19 ቀን 1995 ዓ.ም. እስከ ሐምሌ 26 ቀን 1995 ዓ.ም. በዩ .ኤስ አሜሪካ በሜሪላንድ ክፍለ ሀገር በሮክቪል ከተማ ተካሂዷል።

በዚህ አገር አቀፍ ጉባዔ ላይ 15 የተቃዋሚ የፖለቲካ  ድርጅቶች ተወካዮች ተካፋይ ሆነዋል።

ጉባዔው ኢትዮጵያ አሁን የምትገኝበትን  የፖለቲካ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች በጥልቀት መርምሯል። እንዲሁም ባለፉት የትግል ዓመቶች ተቋቁመው የነበሩት የተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረቶችና  ቅንጅቶች የታለመላቸውን ግብ ሳይመቱ የቀሩባቸውን ሁኔታዎች አጢኗል። ከዚህም በመነሳት አገራችንን አሁን ከምትገኝበት የችግር ማጥ ለማውጣት የሚቻልበትን የትግል አቅጣጫና የአፈጻጸም ስልቶች በተገቢው መንገድ ቃኝቷል።

በመሣሪያ ኃይል የሥልጣን እርካብ የተቆናጠጡ የኢሕአዴግ ቡድኖችና በእነሱም የተመሠረተው መንግሥት የኢትዮጵያን አንድነት የሚጻረሩ እርምጃዎች ወስደዋል፥ የሀገሪቱም ሉዓላዊነት እንዲደፈር አድርገዋል፥ የሀገሪቱንም አስተዳደር በቋንቋ ክልሎች በማዋቀር ለእርስ በርስ ግጭት እንድትዳረግ አድርገዋል። የሀገሪቱን የኤኮኖሚና የሶሻል መዋቅር በማዳከም የሕዝቧ የኑሮ ደረጃ ከዓለም የመጨረሻውን የድህነት እርከን እንዲይዝ በማድረግ የፈጸሟቸው አፍራሽ ተግባራት ሀገሪቷንና ሕዝቧን አሳፋሪና አስደንጋጭ ከሆነ የውርደት ማጥ ውስጥ ጥለዋል። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ አራተኛው ለመኖር የዕለት ደራሽ እርዳታ ጠባቂ ሆኗል። በአገሪቱ ውስጥ የተንሰራፋው ድህነት ከዕለት ወደዕለት በከፋ መልኩ እየተስፋፋ በመሄዱ ከሀገሪቱ ሕዝብ 14 ከመቶ የሚሆነው ከዓመት ዓመት የዕለት ዕርዳታ ጠባቂ ሆኗል። አስቸኳይ የማስተካከያ እርምጃ ካልተወሰደ በቀር ይህ ቁጥር በፍጥነት እያደገ እንደሚሄድ በመረጃ ተረጋግጧል። በመንግሥት በኩል በሚወሰዱ የጥፋት ድርጊቶች ከሀገሪቱ ሕዝብ 70 በመቶ የሚሆነው ዜጋ በድህነት ቀንበር ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል። በአጠቃላይ ከሃያ ዓመት በፊት 190 ዶላር የነበረው የነፍስ ወከፍ ገቢ በአሁኑ ጊዜ ወደ 89 ዶላር በማሽቆልቆሉ የሀገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች እንዲያዘቀዝቅ አድርጎታል።

የኤች አይ ቪ በሽታ ሥርጭት ከተስፋፋባቸው አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ የመጨረሻውን አስከፊ ደረጃ ይዛለች። በዚህ አሰቃቂ በሽታ ላይ እስቸኳይ የመከላከል እርምጃ ካልተወሰደ በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ከሕዝቧ 18 በመቶ የሚሆነውን እንደሚያወድም ጉባዔው በቂ ግንዛቤ አግኝቷል።

በዘመነ ኢሕአዴግ ወባና ኤች አይቪን የመሳሰሉ በስፋት ሕዝባችንን ያጠቁ በሽታዎች በሀገሪቱ ውስጥ እንዳይስፋፉ ቁጥጥር ባለመደረጉ አምራች የሆነው የሀገሪቱ ወጣት ኃይል በአስፈሪ ቁጥር በሞት ጎዳና ውስጥ ከመገኘቱም በላይ፥ የተማረው ወገን ሳይቀር በሥራ አጥነት ቀንበር ውስጥ በገፍ በመውደቁ በሀገሪቱ ዜጎች የተስፋ መቁረጥና የስደት መንፈስ ጎልቶ እንዲታይ አድርጎታል።

ለማንኛቸውም የልማትና ዕድገት ሥራ እንቅፋት የሆነው የአገዛዙ ንቅዘትና ምግባረ ብልሹነት አሳፋሪ በሆነ ደረጃ በመከሰቱ ለዜጎችም ሆነ ለባዕዳን ኢንቬስተሮች ተስፋ አስቆራጭ ሆኗል፡፡

ከላይ ባጭሩ የተዘረዘሩትና ያልተዘረዘሩት ሰው ሠራሽ ችግሮች በገዢው ፓርቲና መንግሥት ብልሹ አስተዳደርና የሕዝብ ተጠያቂነትንና ኃላፊነትን መሸከም ያለመቻል፥ አገሪቱን በአገርነት እንድትቀጥል ከማያደርጉ የከፉ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንድትወድቅ አድርገዋታል፡፡ ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ምክንያት የሆነውና በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን የያዘው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ከሥልጣን እንዲወገድ ማድረግ አማራጭ የሌለው መሆኑን ጉባዔው አረጋግጧል፡፡

እኛ በሜሪላንድ ክፍለ ሀገር በሮክቪል ከተማ የተሰበሰብነው 15 የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች ኢሕአዴግን በሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል ለማስወገድ፥ አገሪቱንም ከወደቀችበት የድኽነትና ኋላ ቀርነት ማጥና ከአምባገነን አገዛዝ አዙሪት ውስጥ ፈጥኖ ለማውጣት፥ በሀገሪቱም በሕዝብ ነፃ ምርጫ የሚቋቋም ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ለማቋቋምና ቀጣይነት የአገር ግንባታ ለማካሄድ በሰላማዊ መንገድ የሥልጣን ሽግግር መደረግ እንደሚኖርበት አምነናል፡፡ ሕዝቡ በየመስኩ የሚያደርገውን ሠላማዊ ትግልና የተቃዋሚ ድርጅቶችን እንቅስቃሴዎች የሚያስተባብር የኅብረት ግንባር በመፍጠርና የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን በሚከተሉት የጋራ አቋሞች ላይ ተስማምተናል፡፡

## ሀ. አጠቃላይ

1. ለአገሪቱ ችግሮችና ለውድቀቷ ተጠያቂ የሆነው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት በሠላማዊ ሕዝብ የተባበረ ትግል እንዲወገድና በምትኩ በሕዝብ ነፃ ምርጫ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣኑን እንዲረከብ ለማድረግ የሚያስችል፥ ትግላችንን የሚመራና የሚያስተባብር "የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት" (ኢዴኃኅ) በሚል ስም የሚንቀሳቀስ ኅብረት ፈጥረናል፡፡ እስካሁን ድረስ ተቋቁመው የነበሩት የኅብረት መድረኮች እንዲፈርሱና በዚህ አካል እንዲተኩ ወስነናል፡፡

2. የሀገሪቱ ዳር ድንበሮች በየማዕዘናቱ መደፈራቸውን በታላቅ ቁጭት በመገንዘብ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ታሪካዊ ግዴታችንን በጋራና በተባበረ የትግል ክንድ ለመወጣት ወስነናል፡፡

3. በሀገሪቱ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፥ ፍትሕና የፍትሕ ሥርዓት እንዲከበር ለማድረግ፥ ሰብዓዊ መብታቸው ከሕግ ውጭ ተደፍሮ በየወህኒ ቤቱ የታጎሩት እነ አቶ አበራ የማነአብ፥ ፊ/መኮንን ዶሪና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ነፃ እንዲወጡ፥ በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት ታፍነው ተወስደው የደረሱበት ያልታወቀ ዜጎችም ወደ ሠላማዊ ኑሯቸው እንዲመለሱ፥ በፖለቲካ ችግሮች ተገደው አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ዜጎች ወደአገራቸው ተመልሰው ለግንባታው አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ለመታገል ተስማምተናል፡፡

4. የሀገሪቱ የውሃ ሀብት (ጅረቶች፥ ወንዞች፥ ሐይቆች ወዘተ...) ለልማት እንዲውልና በሁለገብ አፋጣኝ የልማት እርምጃዎች ሀገሪቱ በምግብ ራሷን ችላ ሕዝቡን ከረሃብ ነፃ ለማውጣት ቆርጠን እንታገላለን፡፡ ለዚህም

በየአቅጣጫውና በተናጠል የምናደርገውን ሠላማዊ ትግል አስተባብረን ምቹ የሆነ የፖለቲካና የአስተዳደር መዋቅር በሕዝብ ነፃ ውሳኔ በማስፈን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝቡን ከጨቋኝና አምባገነን ሥርዓት ቀንበር ማላቀቅ እንዳለብን ተስማምተናል።

5. የኢንዱስትሪውና የእርሻው፥ የንግዱና የማኅበራዊ ኑሮው ግንባታ እርስ በርሱ ተደጋግፎና አንዱ ሌላውን በሚያሳድግና ለሥራ አጡም ዜጋ የሥራ መስክ በሰፊው ለማስገኘት በሚችልበት ሁኔታ እንዲራመድ፥ በነፃ ሚዛናዊ ውድድር እውን በሆነበት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የአገር ውስጥ ሀብት በቂ ጥበቃ በሚያገኝበት ሁኔታ፥ የውጭው ገበያና ኢንቬስትመንት ለሀገሪቱ ዕድገት የራሱን ሚና እንዲያበረክት ለማድረግ በጋራ ቃል ገብተናል።

6. ሕዝባችንን በገፍ እየቀሰፈ ያለውን ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመከላከል፥ በበሽታው የተያዙትንም ለመንከባከብ የሚያስችሉ እርምጃዎች ለመውሰድና በበሽታው ምክንያት እናት አባታቸውን ያጡትን ሕፃናትና ወጣቶች ለመንከባከብ የሚያስችሉ እርምጃዎች በአፋጣኝ መወሰድ እንዳለባቸው ተስማምተናል።

7. በሀገሪቱ ውስጥ በነፃ የመደራጀት፥ ሐሳብን በነፃ የመግለጽ፥ ያልተገደበ የሰብዓዊ መብት በተግባር እንዲገለጽና አንዱ የዴሞክራሲ ዘርፍ የሆነው የነፃው ፕሬስ ተቋም ነፃነቱ ተከብሮ ለሀገሪቱ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የሚያደርግ የሕግ ዋስትና ለማስገኘት እንታገላለን።

8. የፆታ እኩልነት እንዲከበር ከማድረግ አኳያ ሴቶች ለሀገሪቱ ግንባታና ለመልካም ባሕላችን ዕድገትና ለፆታ እኩልነት የሚያደርጉትን ሁለገብ ትግል ለማጠናከር እንደየፍላጎታቸው ሴቶችን በየፓርቲዎቹ የማደራጀትን ሥራ በንቃት ለማራመድ ተስማምተናል።

9. የሞያ፥ የፆታና የወጣቶች ማኅበራት በነፃ ተደራጅተው ለአገራቸው ሁለገብ ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ተስማምተናል።

10. የተማሩ ዜጎች ስደት አገሪቱን በአስከፊ ደረጃ የወላድ መካን እያደረጋት ስለሆነ በዚህ አንጻር የተከማቹትን ችግሮች የሚያስወግዱ ተከታታይ መፍትሔዎች በሥራ ላይ እንዲውሉና የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን በሰፊው በአገር ግንባታው መስክ የሚሰማሩበትን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠርና በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ተስማምተናል።

11. የሕወሓት/ኢሕአዴግ የትምህርት ፖሊሲ የአገሪቱን የትምህርት ሥርዓት አዘቅት ውስጥ ከጣለበት ለማንሣት የሚያስችል፥ በመስኩ ተመራማሪዎች፥ በመምህራንና በወላጆች የተመከረበትና እነሱን የሚያሳትፍ ሕዝባችንን የዘመኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚያድርግ በአገሪቱ ፍላጎትና የዕድገት አቅጣጫ አኳያ የሚግከል የትምህርት ፖሊሲ ተነድፎ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ትግላችንን እናስተባብራለን። እስከዛሬ በመምህራንና በማህበራቸው በኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ላይ የተፈጸመውን ግፍና በደል በጥብቅ እናወግዛለን።

12. የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃ ምርጫ መብቱን የሚቀዳጅበት፥ የዓለም አቀፍ የምርጫ ሕግና ሥርዓትን ባሟላ የምርጫ ሕግ መሠረትና፥ በሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎ በሚቋቋምና የሁሉንም ይሁንታ ባገኘ ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽን አማካይነት እንዲሁም በዓለም አቀፍና አገር በቀል ገለልተኛ ወገኖች አስተባባሪነትና ታዛቢነት የሚካሄድ ነፃ ምርጫ እንዲደረግና ሕዝብም በነፃ መብቱ ተጠቅሞ መሪዎቹንና ተወካዮቹን የሚመርጥበት ዴሞክራሲያዊ ሂደት እንዲኖር ለማድረግ ከወዲሁ ትግላችንን ለማስተባበር ተስማምተናል፡፡ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል አላስፈላጊ ውድድርን ለማስወገድ ኅብረቱ በሚያወጣው ስልትና መመሪያ መሠረት በጋራ ሥልጣንን ለማስገኘት የሚያስችል ምርጫ ለማካሄድ የጋራ አቋም ወስደናል፡፡

13. በዚህ ጉባዔ ላይ ያልተካፈሉና በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት የሚታገሉ ድርጅቶች የኅብረቱ አባል ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲያመቻች የጋራ አቋም ወስደናል፤ ከዚሁ አኳያ ለአገር ዕድገትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታገሉ ድርጅቶች ሁሉ የኅብረቱ አባል እንዲሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

14. የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተጋረጠበት አጠቃላይ አደጋ ለመዳን በየአቅጣጫው በሠላማዊ ትግሉ ውስጥ እስከዛሬ ከሚያደርገው በበለጠ በባለቤትነት ተካፋይ እንዲሆንና ለትግሉ መፋፋም አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ሕዝቡ በመረጠው ፕሮግራምና የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ የኅብረት ግንባሩ በሚቀይሰው ሠላማዊ የትግል መስመር በመሰለፍ አሳፋሪና ዘግናኝ ከሆነው ሁኔታ ውስጥ ራሱን ለማውጣት እንዲንቀሳቀስ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

15. የመከላከያ ሠራዊቱ፥ የፖሊስና የደህንነት ኃይሎች ሁሉ መሣሪያቸውንና ኃይላቸውን ለገዢው መደብ ሕልውና በማዋል ሕዝብን በመበደልና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማሳደድና በማፈራረስ ሥራ ላይ ከማዋል ይልቅ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ክንድና አለኝታ መሆናቸውን አምነው ለአገሪቱ ደህንነት የሚደረገውን ሠላማዊ ትግል በተግባርም በሞራልም እንዲያግዙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ከአንግዲህ በሕዝብ ላይ በደል እንዳይፈጽሙም እንመክራለን፡፡

16. የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅ የሆኑ ሕዝቦች መንግሥታትና በአጠቃላይም ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ ሕዝብና ሀገር ዘላቂ፤ መንግሥት ግን ጊዜያዊ መሆኑን በመገንዘብ አገሪቱንና ሕዝቧን ወደ ከፋ ውድቀትና መቃብር ለማውረድ ተግተው እየሠሩ ያሉትን ገዥውን ድርጅትና መንግሥቱን ከማጠናከር ይልቅ፥ በአገሪቱ ዘላቂ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲገነባ ለማድረግ የምናደርገውን ሠላማዊ ትግል በማገዝ በኢሕአዴግ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ እንዲያደርጉ በድህነት፥ በበሽታና በኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በተጎሳቆለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ጥሪያችንን እናቀርብላቸዋለን፡፡

## <u>ለ. የሀገር ሉዓላዊነትን በተመለከተ የተላለፈ፤</u>

ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ድንበር በተመለከተ የሕዝብን ፍላጎትና ታሪክን በተፃረረ መንገድ እርምጃ ሲወስድ መቆየቱን ጉባዔው የጋራ ግንዛቤ ወስዷል። ኢትዮጵያን ያለባሕር በር ያስቀረው የተበላሸ የሕወሓት /ኢሕአዴግ ፖሊሲ የሀገሪቷን ጥቅም አሳልፎ በመስጠት ሲያስመዘብራት ከቆየ በኋላ ለሻዕቢያ ወረራ በር ከፋች ሆኗል። ከዚህ የተነሣ በተከተለውም ጦርነት ከመቶ ሺ ያላነሰ ሕይወት ከመጥፋቱም በላይ መጠኑ ከፍ ያለ ገንዘብና ንብረትም የባከነ ሲሆን፥ ወያኔ ኢሕአዴግ የባድሜና አዲ-ኢሮብ ሰፋፊ መሬቶቻችንን ለሻዕቢያ አሳልፎ መስጠቱ እነሆ ገሃድ ሆኗል። በሰሜን ምዕራብ ጐንደርና በጋምቤላም ገፅ ለሌላ ወገን አሳልፎ እየሰጠ መሆኑ በተደጋጋሚ በመከሰት ላይ ነው።

ጉባዔው ሕወሓት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ግዛቶች አሳልፎ በመስጠት በሀገሪቷ ላይ ያደረሰውን ከባድ ጉዳት መርምሮ ሕወሓት/ኢሕአዴግን አውግዟል። የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፥ ዳር ድንበርና ወሰን ለማስከበር ሕይወታቸውን ለሰጡትና እየሰጡም ላሉት አድናቆቱን እየገለጸ፥ ሁሉም ዜጋ የሀገሩን ሉዓላዊነት ለማስከበር እንዲታገል ጥሪ አስተላልፏል። በሕወሓት/ ኢሕአዴግ ደንታ ቢስነት የተነሣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚነካውን የዓለም-አቀፍ የሄግ ፍርድ ቤት ውሳኔ ማንም ሀገር ወዳድ ዜጋ የሚቀበለው አለመሆኑንም ጉባዔው በጥልቀት ተገንዝቧል። ይህንን የሀገራችንን ሉዓላዊነት የተፃረረና የኅወሓት/ኢሕአዴግ ሴራ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነካ ውሳኔ በመቃወም ሁሉም በዲፕሎማሲያው መስክና በሌላም ዘርፍ በሀገር ወዳዶች እየተካሄደ ያለውን ትግል እንዲያግዝና ተቃውሞውንም አስተባብሮ እንዲያሰማ ጉባዔው አሳስቧል። ኢዴኃኅም በዚሁ ጥያቄ ዙሪያ :-

1) ለባድሜና አዲ-ኢሮብ አካባቢ ሕዝብ ሙሉ ድጋፉን እንዲሰጥ፥

2) በሰሜን ጎንደርና በጋምቤላ አቅጣጫዎች ለሌላ ወገን አሳልፎ በመሰጠት ላይ ስላሉት አካባቢዎችና ስለተደረጉት የአገር ክህደት ደባዎች ተቃውሞውን በማፋፋም እንዲገፋበት፥

2) በኢትዮጵያ ላይ የተወሰነውን ሕገወጥ ውሳኔ በተመለከተ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ተቃውሞን ለማሰማት ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እንዲደረግ፥

4) በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ለግዳጅ ተሰማርተው ከፍተኛ ጀግንነት በመፈጸም ላይ እያሉ በሻዕቢያ የተማረኩትን የሠራዊቱን አባላትና ሌሎች ዜጎች ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶ እንዲከታተልና የሕወሓት/ኢሕአዴግን የሚወገዝ አቋምና ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊት ሳያሰልስ እንዲያጋልጥ ጉባዔው ኃላፊነት ሰጥቶታል።

## ሐ. የሰብዓዊ መብት ረገጣና የፖለቲካ እስረኞችን በተመለከተ፤

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ምንም እንኳን በዓለም-አቀፍ ደረጃ መሠረታዊ የተባሉ ሰብዓዊ መብቶችን አከብራለሁ ብሎ ቢመጻደቅም የኢትዮጵያውያንን ሰብዓዊ መብት ሲረግጥ መቆየቱ ይታወቃል። የጅምላ ጭፍጨፋ፥ ሕግና ሥነ-ሥርዓትን የተፃረረ እስራት፥ የፍትሕ መጓደል፥ ግርፋትና ማሰቃየትን እንዲሁም ግድያዎችን በመፈፀም ዘወትር ሥርዓተ አልበኛነትን ያስፋፋ መንግሥት ነው። እንዲሁም የመጻፍና የፕሬስን መብት በማቀብና የፍትሕ ሥርዓቱን በመቆጣጠር የዜጎችን መብት በሰፊው የተጻረረ ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ በብዙ ቦታዎች ለተከሰቱትና አያሌ ሕይወት ላጠፉት የእርስ በርስ ግጭቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠያቂነት አለው። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን በምስጢርና በይፋ በሚታወቁ እስር ቤቶች ውስጥ አስሮ በማሰቃየትና ብዙዎችም ከተያዙ በኋላ ደብዛቸው በማጥፋት መሠረታዊ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ባለማቋረጥ ረግጧል።

ጉባዔው ይህን ሁሉ ካጤነ በኋላ ሕወሓት/ኢሕአዴግ እያካሄደ ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ በጥብቅ አውግዟል። የፖለቲካ እስረኞች አለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንዲፈቱና ደብዛቸው የጠፋውንም በተመለከተ አገዛዙ ምላሽ እንዲሰጥ፥ እየጠየቀ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበሩ በሀገራችን ውስጥ ላሉ ችግሮች ፖለቲካዊ መፍትሔ ለማምጣት ወሳኝ መሆኑን ጉባዔው በአጽንዖት ተገንዝቧል። ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ለማስከበር ሕዝቡ ከኅብረት ግንባሩ ጐን በመሆን አስፈላጊውን ትግል ማድረግ እንዲቀጥልም ኢ.ዴ.ኃ.ኅ ጥሪውን ያቀርባል.።

## መ. የስደተኛን ሰቆቃ በተመለከተ፤

የአምባገነኑን የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት አፈና እያመለጡ ወደ ጐረቤት ሀገሮችና ወደ ሌሎችም ሀገሮች የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን እየደረሰባቸው ያለው መከራ በጣም የከፋ መሆኑን ጉባዔው አጢኖ የስደተኞች መብት እንዲከበር ተገቢውን ዋስትና እንዲያገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያሉበት ከኅብረቱ ጎን ሆነው እንዲታገሉ ጥሪ አስተላልፏል። ስደተኞቹ በሚገኙባቸው ሀገሮች በተለይም በሱዳን፥ በኬንያ፥ በጅቡቲ፥ በየመንና በደቡብ አፍሪካ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ኮሚሽን ባለሥልጣኖች የስደተኞቹን መብት ለማስከበር የሚያደርጉት ጥረት በቂ እንዳልሆነ ጉባዔው ተመልክቷል። በእነዚህ ሀገሮችም ሁሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ኤምባሲዎችና ሠራተኞች የስደተኞቹን መከራ ለማባባስና ሕይወታቸውንም አደጋ ላይ ለመጣል እየጣሩ መሆናቸውን ጉባዔው ተረድቷል። ስለሆነም በየሀገሩ ያሉት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ኮሚሽን ቢሮዎች የኢትዮጵያ ስደተኞችን መብት እንዲያስከብሩ በጥብቅ ያሳስባል። ስደተኞቹ የሚገኙባቸው ሀገሮች መንግሥታትም ከሕወሓት/ኢሕአዴግ አብረው ስደተኛውን ማሰቃየትን አቁመው የስደተኞቹን መሠረታዊ ጥገኝነት የማግኘት መብታቸውንና ሰብዓዊ መብታቸውን እንዲያከብሩ ይጠይቃል። በአንጻሩም ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵውያን የስደተኞቹ ሰቆቃ እንዲያከትም በሚካሄዱ ጥረቶችና ዘመቻዎች ሁሉ ንቁ ተሳትፎ እንዲያሳዩ ጉባዔው ጥሪ አስተላልፏል።

## ሠ. የኢትዮጵያ ሴቶችን ሰቆቃ በተመለከተ፤

የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት የሴቶችን ችግርና መከራ የሚያባብስ መሆኑ በሁሉም ዘርፍ ታይቷል። አጠቃላይ ድህነትና የመብት ረገጣው ብዙሃኑን ሴቶች በገጠርም ሆነ በከተማ በተቀዳሚ ደረጃ እያጠቃ መሆኑ ይታያል። በኤችአይቪ ኤድስ እየረገፈ ካለው ዜጋ ብዙሃኑ ሴቶች ናቸው:: ለአቅመ-ሔዋን ያልደረሱ ወጣት ሴቶች ጭምር ለሴተኛ አዳሪነትና ከባሕል ውጪ የሆኑ አፀያፊ ተግባሮችን እንዲፈጽሙ ወደሚገፋፉ ሁኔታዎች ተወርውረዋል። ብዙ ሺ ወጣት ሴቶች ለዘመናዊ ባርነት ወደ መካከለኛ ምሥራቅ መሄድ ተገደው በልዩ ልዩ ሀገሮችም ከፍተኛ በደልና ወንጀል እየተፈጸመባቸውና እየተሰቃዩም ናቸው:: እድሜያቸው የማይፈቅደውንና በሕግ የተከለከለን ከባድ ሥራ እየሠሩ ካሉ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ሕፃናት ውስጥ ብዙዎቹ ሴቶች ናቸው::

ምንም እንኳን የሴቶችን ሁኔታ ለመለወጥና ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት በመላ ሀገሪቷ የዴሞክራሲን ሥርዓት ከማስፈን ጋር የተያያዘ ቢሆንም፥ ከወዲሁ የሴቶችን ሰቆቃ ለመቀነስና አንዳንዶቹንም ለመቅረፍ ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች እንዳሉ ጉባዔው ተገንዝቧል። የሴቶችንና የሕፃናትን መብት ሕወሓት/ኢሕአዴግ እንዲያከብር መታገል፥ የሴቶችን መብት ለማስከበር የሚታገሉ ተቋማትን ማገዝና መደገፍ፥ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፏቸው እንዲጨምር መጣር፥ የሴቶችን ወደ ዘመናዊ ባርነት መላክ ሂደት መቃወም፥ ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው:: ጉባዔው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት የሴቶችን መከራ ያባበሰና ያስፋፋ መሆኑን በሚገባ በማጤንና በማውገዝ ሴቶችን ለትግሉ ቀስቅሶ በማሳተፍ ሁኔታውን

ለመለወጥና የሴቶችን መብት ለማስከበር ሴቶች ራሳቸው በቅድሚያ እንዲታገሉት ለማድረግ ሁለገብ ጥረቱን መጠናከር እንዳለበት ጉባዔው አምኖበታል፡

## ረ. በነፃ ፕሬስ ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት በተመለከተ፤

የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጦች የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከተመሠረተ ጀምሮ ለፕሬስ ነፃነት ያካሄዱት ትግል የሚደነቅና በሀገራችን ለዴሞክራሲ እየተደረገ ላለው ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለ ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ የፕሬስ ነፃነትን የሚገድብ ሕግ አውጥቶ በነፃ ጋዜጦች ላይ አሉታዊ ድርጊቱን ሲፈጽም ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ይበልጥ አፋኝ የሆነ የፕሬስ ሕግ ለማወጅ በመንደርደር ላይ ይገኛል።

ጋዜጠኞች የፕሬስ ነፃነት ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታ ሥራቸውን እንዳይሠሩ እንቅፋት እየተፈጠረባቸው፥ እየታሰሩና እየተሳደዱ ሲሰቃዩ መቆየታቸውን ጉባዔው በማጤን ለነፃ ጋዜጠኞችና ለማኅበራቸው ፍትሐዊ ትግል ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል። ጋዜጠኞቹ ላይ አፈናና ዕመቃ እያካሄደ ያለውንም የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ጉባዔው አጥብቆ እያወገዘ ሕጋዊ ተብሎ ሊፀድቅና ሊታወጅ እየታሰበ ያለውንም የፕሬስ ሕግ ኢ-ዴሞክራሲያዊ በመሆኑ በሥራ እንዳይውል ለማድረግ ትግሉ እንዲቀጥል ለሁሉም የነፃው ፕሬስ ተቆርቋሪዎችና ለሕዝቡ ጥሪውን ያቀርባል።

ጉባዔው ለፕሬስ ነፃነትና ለዴሞክራሲያዊ መብት እየታገሉ ያሉትን ነፃ ጋዜጠኞች እያደነቀ ሙሉ ድጋፉን ይሰጣቸዋል። በዓለም-አቀፍ ደረጃም ድጋፍ እንዲያገኙ ኅብረቱ የበኩሉንም ሙሉ ጥረት እንዲያደርግ ወስኗል።

በሞኖፖል መልክ በመንግሥትና በሕወሓት/ኢሕአዴግ የተያዙት የሚዲያ ዘርፎችም (ሬዲዮ፥ ቴሌቪዥን ወዘተ...) በግል ንብረትነት በሚዲያው ዘርፍ ሊሠማሩ ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ክፍት መሆን እንዳለባቸው ጉባዔው አምኗል።

## ሰ. በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጭፍጨፋ በተመለከተ፤

የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለሥልጣን ከበቃ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በየአቅጣጫው እያደረሰ ያለው ፍጅት በታሪካችን ዘግናኝ ምዕራፍ የጻፈና አመርቃዥ ቁስልም እየፈጠረ ያለ ነው። በአረካ፥ በወተር፥ በአርባጉጉ፥ በአደባባይ ኢየሱስ፥ በምሥራቅ ወለጋ፥ በአምቦ፥ በአዲስ አበባ ውስጥ በአንዋር መስጊድ፥ በተደጋጋሚ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና በሌሎችም ተማሪዎች ላይ የተፈጸሙትን ጭፍጨፋዎች፥ እንዲሁም በእብሪት በመነሳሳት በአሰቃቂ ደረጃ በአዋሳ፥ በቲፒ፥ በጉጂና ጌዲዮ፥ በሸኮና መዠንገር እንዲሁም በልዩ ልዩ የደቡብና ሌሎችም ክፍሎች የተፈጸሙትን ፍጅቶች ጉባዔው በጥብቅ ይኮንናል። ሕወሓት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያውያ ሕዝብ ማጥቃትና ማስጠቃት ከጀመረ ውሎ ያደረ ሲሆን በተለይም የጋምቤላና የአፋርን ሕዝብ ከራሱ አልፎ ለባዕዳንም ጥቃት አጋልጧል።

በመሆኑም ጉባዔው በተለያዩ ጊዜያት በሀገሪቱ ስፍራዎች ሕዝብን በመፍጀት ላይ የተሰማሩት የሕወሓት/ኢሕአዴግ ካድሬዎችና ባለሥልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡና በግፍ የታሰሩትም ንጹሐን ከእሥር እንዲፈቱ እየቀረበ ያለውን የሕዝብ ጥያቄ ጉባዔው ይደግፋል።

ጉባዔው በሕወሓት፥ በሻዕቢያና በታጠቁ የሱማሌ አንጃዎችና በአንዳንድ የአካባቢው መንግሥታት እየተደገፉ ጥቃት በሚፈጽሙ ታጣቂዎች በአስከፊ ሁኔታ እየተጠቃ ያለውን

የአፋር ሕዝብ ሙሉ በሙሉ እየደገፈ ፀረ-አፋር እርምጃ እየወሰዱ ያሉትን ኃይሎች ያወግዛል።

በአጠቃላዩም በሕወሓት/ኢሕአዴግ በተጠቁና እየተጠቁ ካሉት ወገኖቻችን ጐን በመቆም ለመብታቸው መከበር የሚያደርጉትን ፍትሐዊ ትግል ኢዴኃኅ እንዲደግፍ ጉባዔው መመሪያ ሰጥቶታል።

## ሸ. የኤድስ በሽታ መስፋፋትና ኃላፊነት በተመለከተ፤

ቀሳፊው የኤድስ በሽታ በሀገራችን ተስፋፍቶ ከ 4 ሚሊዮን ያላነሡ ሕዝብን አጥቅቶ ከአንድ ሚሊዮን ተኩል በላይ ሕይወት ማጥፋቱ ብቻ ሳይሆን በአስደንጋጭ ደረጃም እየተስፋፋ መሆኑን ጉባዔው ተገንዝቦ ይህንን ቀሳፊ በሽታ ለመቋቋም የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከወረርሽኙ አደጋ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑን አጢኗል።

ሥራአጥነት፥ ድህነት፥ የአደንዛዥ ዕፅና አልኮል ልምድ መስፋፋት፥ ፀረ-ኤድስ ትምህርታዊ ዘመቻ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚገባው መንገድና ደረጃ አለመደረጉ፥ ወዘተ የበሽታውን መስፋፋት አግዘዋል። ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአፋዊ ደረጃ በበሽታው ላይ የዘመተ ቢያስመስልም ይህ በተግባር ሃቅ ካለመሆኑም ሌላ፥ የሀገሪቷን የጤና ተቋሞች ከማዳከሙ ጋር ተዳምሮ የበሽታውን መስፋፋት አባብሶታል። ስለሆነም የኤድስ በሽታ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ከተጋረጡት ከፍተኛ አደጋዎች ውስጥ አንዱና ምናልባትም ከፍተኛው ነው።

በመሆኑም ጉባዔው ሕወሓት/ኢሕአዴግ የጤና ተቋሞችን በማሽመድመድና በማዳከም በኤድስ ላይ አስፈላጊውን ዘመቻ አለማድረጉን ተገንዝቦ እነዚህን ተግባሮቹንና ግድፈቶቹን እያወገዘ ይህንን በሽታ ለመቋቋም ደግሞ ሁሉም ዜጋ በጋራ እንዲዘምት ጥሪ ያደርጋል። በሽታው ወጣቱን ክፍል፥ ከተሜውንም ገጠሬውንም በተለይ ደግሞ ከ15-49 ዓመት ዕድሜ ያለውን ከተሜ በስፋት እያጠቃ በመሆኑ ኢ.ዴ.ኃ.ኅ ባለው አቅም ሁሉ በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰፊ ትምህርታዊ ዘመቻ በማካሄድ የሀገሪቷን አምራች ኃይልና ወጣት እያወደመ ያለውን በሽታ ለመከላከል መጣር እንዳለበት አሳስቧል። ወጣቱ ክፍልም ለበሽታው ስርጭት ከሚያባብሱ አልባሌ ጠባዮችና ልምዶች እንዲርቅ ጥሪ ያደርጋል። ፀረ-ኤድስ ግብረ-ኃይል በማቋቋምም ኅብረቱ እንዲንቀሳቀስ ኃላፊነት በጉባዔው ተሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበረ ትግል ያሸንፋል!

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ ተካፋዮች

ሐምሌ 28 ቀን 1995 ዓ.ም.

ሮክቪል ሜሪላንድ

*የአፋር አብዮታዊ አንድነት ግምባር፥ የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት፥ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ፥ የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ም/ቤት፥ የኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ፥ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት፥ የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግምባር፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ፥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ፥ የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግምባር፥ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ፥ የኦሮሞ ሕዝብ ነፃነት ድርጅት- ኢብሶ፥ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት፥ የትግራይ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ትብብር*